መሠረት፣ 3ኛ. በሠራተኛ አነሳሽነት የሥራ ውል ሲቋረጥ 4ኛ. በአሠሪ አነሳሽነት የሥራ ውል ሲቋረጥ

## በአሰሪዎችና በሠራተኞች መፈጸም የሌለባቸው ሕገ ወጥ ድርጊቶች

የሚከተሉትን መፈፀም ለማንኛውም አሰሪ ህገወጥ ድረጊት ነው

- ሰራተኛው መብቱን እንዲያስከብር በማንኛውም አኳኋን መብቱን ማደናቀፍ ወይም መብቱን በማስከበሩ በሰራተኛው ላይ እርምጃ መውሰድ፤
- ለሴት ሠራተኞች በፆታቸው ምክንያት የክፍያ ልዩነት ማድረግ፤
- የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሚቃረን አኳኋን የስራ ውል ማቋረጥ፤
- ሠራተኛውን የሰራተኛ አባል እንዲሆን ወይም እንዳይሆን፣ ከሆነ በኂላ እንዲያቋርጥ ወይም በማህበር ምርጫ ወቅት ለአንድ ተወዳዳሪ ድምጹን እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ በኃይልም ሆነ ሌላ ማንኛውም መንገድ ማስገደድ፤
- ሰራተኛን በህይዎቱ ላይ አደጋ በሚያደርስ አኳኋን እንዲሰራ ማድረግ፤



- በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት እና በሌላም ሁኔታ በሠራተኞች መካከል ልዩነት ማድረግ፤
- 

የሚከተሉትን መፈፀም ለማንኛውም ሠራተኛ ህገ ወጥ ድርጊት ነው፡፡

- በሕይዎትንና ንብረትን አደጋ ላይ የሚጥል ድርጊት ሆን ብሎ በሥራ ቦታ ላይ መፈፀም፤
- አሰሪው በግልፅ ሳይፈቅድ ከስራ ቦታ ንብረት መውሰድ፤
- በስራ ላይ ሰክሮ መገኘት፤
- ሕግ ሲያስገድድ ወይም አሰሪው በበቂ ምክንያት ሲጠይቅ ከኤች አይ ቪ ኤድስ ምርመራ በስተቀር ማንኛውንም የጤና ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆን፤
- ስለ ደህንነት ጥበቃና ስለ አደጋ መከላከል የወጡ የሥራ ደንቦችን አለማክበርና አስፈላጊ የሆኑትን የአደጋ መከላከያ ጥንቃቂዎች ለመውሰድ ፈቃደኛ አለመሆን፡፡

**ለበለጠ መረጃ**

ማዕከላዊና ምዕራብ ጎንደር ዞኖች ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያዎችን ያነጋግሩ
ስልክ፡
ፓ.ሣ.ቁ፡



# በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በሰሊጥ መረብ ለሚገኙ አሰሪና የቀን ሰራተኞች የስራ ግንኙነትን በተመለከተ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተዘጋጀ

# አሰሪና ሰራኛ ጉዳይ አዎጅ
# ቁጥር 377/1996

አሰሪና ሰራተኞች የስራ ግንኙነታቸውን መሰረታዊ በሆኑ መብቶችና ግዴታዎች ላይ ተመስርተው እንዲያካሂዱ ይረዳ ዘንድ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ታውጇል። በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በሰሊጥ ንዑስ ዘርፍ የሚሰሩ የአሰሪና ሰራተኞችን ግንዛቤ ለማዳበር ከዚህ አዋጅ ውስጥ የሰራተኛው መብትና ግዴታዎች፣ የአሰሪው መብትና ግዴታዎች እንዲሁም የስራ ውልን በተመለከተ የሰፈሩ መሰረታዊ ነጥቦችን በዚህ ጹሑፍ እንደሚከተለው እናቀርባለን።

## የሠራተኛው ግዴታዎች

- በስራ ውሉ ላይ የተመለከተውን ሥራ ራሱ የመስራት፤
- በሥራ ውሉና በስራ ደንቡ መሠረት በአሠሪው የሚሰጠውን ትእዛዝ የመፈጸም፤
- ለሥራ የተሠጡትን መሳርያዎችና እቃዎች በጥንቃቄ የመጠበቅ፤
- ለሥራ ብቁ በሆነ የአዕምሮና የአካል ሁኔታ በሥራ ላይ የመገኘት፤
- ራሱንም ሆነ የሥራ ጓደኞቹን አደጋ ላይ የሚጥል፤ የድርጅቱን ጥቅም የሚነካ ሁኔታ ሲያጋጥመው ወዲያውኑ ለአሠሪው የማሳወቅ፤
- የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96፤የሥራደንብና የህግ መመሪያዎችንና ትእዛዞችን የማክበር፤

## የሠራተኛው መብቶች

- ልዩ ልዩ ፈቃዶችን ማለትም የአመት፣ የህመም፣ለቤተሰብ ጉዳይ የሚሠጥ ፈቃድ ወዘተ ያገኛል፤
- በሰባት ቀናት ውስጥ ያልተቆራረጠ የ24 ሰዓት አንድ የዕረፍት ቀን ይኖረዋል፤
- በድርጅቱ የሥራ ሰዓት መሠረት በቀን 8 ሰዓትና በሳምንት 48 ሰዓት ያልበለጠ ይሠራል፤የትርፍ ሰዓት፣ የህዝብ በዓላት፣ የሥራ ስንብት ክፍያና ሌሎች ክፍያዎችን በህጉ መሠረት ያገኛል።
- ሠራተኛው ባአሠሪና በአዋጅ መሠረት የሥራ ውሉን በማስጠንቀቅያ ወይም ያለማስጠንቀቅያ ሊያቋርጥና በተቀጠረ በ45 ቀናት ውስጥ ያለማስጠንቀቅያ የሥራ ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል።

## የአሠሪው መብትና ግዴታዎች

- በሥራ ውሉ መሠረት ለሠራተኛው ሥራ የመስጠትና በሰራ ውሉ በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር ለስራ የሚያስፈልገውን መሳሪያና ጥሬ ዕቃ የማቅረብ፤
- ለሠራተኛው ደመወዙንና ሌሎች ክፍያዎችን በአዎጁ መሰረት የመክፈል፤
- ለሠራተኛው የሚገባውን ሰብዓዊ ክብር የመስጠት፤
- ከስራው ጋር በተያያዘ የሠራተኛውን ደህንነትና ጤንነትን ለመጠበቅና ከአደጋ ለመከላከል የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች ሁሉ የመውሰድና አነዚህንም እርምጃዎች በሚመለከት ረገድ አግባብ ባላቸው ባለስልጣኖች የሚሰጡትን ደረጃዎችና መመሪያዎች የመከተል፤
- የሰራተኛው ጤንነት እንዲመረመር በህግ ወይም በባለስልጣን ግዴታ በሚጣልበት ጊዜ ለምርመራው የሚያስፈልገውን ወጭ የመቻል፡
- ከላይ የተመላከቱትን አግባብ ያላቸውን ዝርዝሮች የተወሰደ ረፍት፣ የህዝብ በዓልና ፈቃድ፣ የሰራተኛው የጤንነት ሁኔታ፣ በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት እና ሌሎችም እንዲያዙ የተወሰኑ ነጥቦችን የሚያሳይ መዝገብ፤
- የስራ ውል በሚቋረጥበት ወይም ሰራተኛው በሚጠይቅበት ማናቸውም ጊዜ ሠራተኛው ሲሰራ የነበረውን የሥራ ዓይነት፣ የአገልግሎት ዘመኑንና ሲከፈለው የነበረውን ደመወዝ የሚያሳይ የምስክር ወረቀት በነፃ የመስጠት፤
- የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን፣ የህብረት ስምምነትን፣ የስራ ደንብንና በህግ መሰረት የሚተላለፉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን ማክበር፤
- በዚህ አዋጅ በመዝገብ እንዲያዙ የተወሰኑትንና ሌሎች በህግ ሚኒስቴሩ የተሰጠውን ተግባርና ስልጣን ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመዝገብ ለመያዝና ሚኒስቴሩ በሚፈልገው ዓይነት ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ የማቅረብ።

## የሥራ ውል

- የሥራ ውል በሶስት መንገዶች ሊያዝ ይችላል፡ ለተወሰነ ጊዜ፤ ለተወሰነ ሥራ፣ እንዲሁም ላልተወሰነ ጊዜ
- የሥራ ውል በተቻለ መጠን በጽሁፍ ቢሆን ይመረጣል፣ ነገር ግን በቃል የተደረገ የሥራ ውል ሠራተኞች በአዋጁ መሠረት የሚያገኙዋቸውን መብቶች አያሳጣም።
- የሥራ ውል የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች ሊይዝ ይገባል፡- የሥራውን አይነት፣ ቦታ፣ የሚከፈለውን የደመወዝ መጠን፤ የሥሌቱን ዘዴ፤ የአከፋፈሉን ሁኔታ እና ጊዜ እንዲሁም ውሉ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ መያዝ አለበት።

## የሥራ ውል መቋረጥ

- በአሠሪው እና በሠራተኛው መካከል ተፈጥሮ የነበረው በሥራ ውል ላይ የተመሠረተ የቅጥር ግንኙነት በአራት አበይት መንገዶች ይቋረጣል፡ 1ኛ. በሥምምነት፣ 2ኛ. በህግ ወይም በህብረት ስምምነት በተደነገገው